# የMedicaidን የእድሳት ሂደት የሚያሳይ ቻርት

## *ሂደቱን ደረጃ በደረጃ መረዳት*

**የእድሳት ሂደቱ ከማብቃቱ በፊት** የ Medicaid/FAMIS ሽፋንዎን አውቶማቲካሊ ለማደስ እንሞክራለን። መደበኛ ውሳኔያችንን እንደገና ስንጀምር እድሳትዎን የምንጀምርበት ወር የተለየ ሊሆን እንደሚችል ልብ ይበሉ – የምንልክልዎን መልእክቶች በንቃት ይከታተሉ!

**ወዲያውኑ የሚታደስልዎ ከሆነ ሽፋንዎ መቀጠሉን** እና የMedicaid የጤና ሽፋንዎ መስተካከሉን የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርስዎታል!

**ወዲያውኑ የማይታደስልዎ ከሆነ በመልእክት ተጨማሪ መረጃ እንደምንፈልግ የሚጠቅስ ጥያቄ ይደርስዎታል።**

**የእድሳት ቅጽ የሚደርስዎ ከሆነ በአፋጣን እርምጃ መውሰድ ይጠበቅብዎታል።** የማብቂያ ቀኑ በሚደርስዎት ቅጽ ላይ ይታተማል። የሚፈልጉ ከሆነ አንዴ ቅጹ ከደረስዎት በኋላ የተለያዩ የማደሻ አማራጮች አሉዎት: 1) ለCover Virginia በስልክ ቁጥር 1-855-242-8282 (TTY: 1-888-221-1590) ይደውሉ፣ 2) ወይም በኦንላይን ወደ CommonHelp.virginia.gov ይግቡ፣ ወይም 3) የወረቀት ቅጹን በአካል ወይም በመልእክት ወይም በፋክስ ይመልሱ። ቅጽዎ እድሳትዎን በስልክ፣ በኦንላይን ወይም በወረቀት ማስገባት እንዳለብዎ የሚገልጽ መረጃ አለው።

**የማረጋገጫ ዝርዝር የሚደርስዎት ከሆነ ዝርዝሩ እድሳትዎን ለማጠናቀቅ ምን እንደሚያስፈልገን በትክክል ይነግርዎታል፤** ለምሳሌ፡ የክፍያዎ ወረቀቶች። ማረጋገጫዎችዎን በአካል፣ ወይም በመልእክት ወይም በፋክስ፣ ወይም በCommonHelp መልሰው መላክ ይችላሉ። ለማብቂያ ቀኑ ትኩረት ይስጡ፣ ሆኖም ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለግዎ ወይም የምንፈልገውን መረጃ ለማግኘት ችግር ካጋጠምዎ የጤና እንክብካቤ ሽፋንዎን በተሟላ ሁኔታ ለመገምገም ከእርስዎ ጋር አብረን ለመስራት ያስችለን ዘንድ እባክዎ በአፋጣኝ እኛን ያግኙን።

**አንዴ ቅጽዎን እና ሁሉንም ማረጋገጫወቾችዎን (አስፈላጊ ከሆነ) ከገመገምን በኋላ ጉዳይዎን እንመረምራለን።** ግምገማዎ ከተጠናቀቀ በኋላ በሽፋንዎ ላይ ምን እንደተፈጠረ የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርስዎታል። ከአሁን በኋላ ብቁ የማይሆኑ ከሆነ ወይም ከሙሉ ወደ ውሱን ሽፋን የሚሸጋገሩ ከሆነና Medicare ከሌሉዎት መረጃዎን በተጨማሪም ለሌላ ሽፋን እና/ወይም ለተሻሻለ የአረቦን ግብር ብድሮች (Advanced Premium Tax Credits) ለMarketplace እንልካለን። እንደተሳሳትን ካሰቡ በደብዳቤዎ ላይ የተዘረዘሩ የይግባኝ መብቶች አሉዎት። በተጨማሪም ሁኔታዎ የሚቀየር ከሆነ ሁልጊዜም በስልክ፣ በኦንላይን ወይም በአካል እንደገና ማመልከት ይችላሉ።

**ቅጽዎ ወይም ማረጋገጫዎችዎ የማይደርሱን ከሆነ የጤና ሽፋንዎ "ባለመታደስ" የሚያበቃ ሲሆን ጥቅማ ጥቅሞችዎ ከመቼ ጀምሮ እንደሚዘጉ የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርስዎታል።** በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ብቁ ላይሆኑ እንደሚችሉ ቢያስቡም እንኳ የወረቀት ስራዎን መልሰው ማስገባትዎ በጣም አስፈሊጊ ነው: 1) ለማያውቁት ሽፋን ወይም ለሌሎች ውሱን ሽፋን ሊያቀርቡ ለሚችሉ ፕሮግራሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ እንዲሁም 2) ጉዳይዎን መገምገም ካልቻልን መረጃዎን ወደ Marketplace መላክ አንችልም። ሆኖም "ባለማደስ" ምክንያት የሚዘጋብዎ ከሆነ ጥቅማ ጥቅሞችዎን ለመገምገም ያስችለን ዘንድ ከተዘጋብዎ በኋላ ቅጽዎን ወይም ማረጋገጫዎችዎን መልሰው የሚያስገቡበት ሶስት ወራት አሉዎት – እንደገና ማመልከት አይጠበቅብዎትም! ከሶስቱ ወራት በኋላ ከእርስዎ ምላሽ የማይደርሰን ከሆነ በድጋሚ ብቁ ስለመሆንዎ ለማየት ካስፈለግዎ እንደገና ማመልከት ይኖርብዎታል።

**ከአሁን በኋላ ሙሉ ሽፋን ለማግኘት ብቁ የማይሆኑ ከሆነ ከቨርጂኒያ Medicaid ውጭ ስላለ ሽፋን ወደ enrollva.org በመግባት ወይም በስልክ ቁጥር 888-392-5132 በመደወል ተጨማሪ ማወቅ ይችላሉ።** Enroll Virginia ለጤና ሽፋን በኦንላይን ወይም በአካል እንዲመዘገቡ የሚረዱዎ ናቪጌተሮች ተብለው የሚጠሩ የሰለጠኑ ረዳቶች አሉት። ረዳቶቹ ዕቅዶችና ወጪዎችን ከቀላል፣ ማንነቱ ያልተገለጸ የኦንላይን መሳሪያ ጋር ማወዳደር - ምን ያክል የገንዘብ እርዳታ ለማግኘትና ለመመዝገብ ብቁ እንደሆኑ ፈልገው ማወቅ ይችላሉ!

